# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## አሣን ውሃ ውስጥ ለመድፈቅ?

በግንቦት ፺፯ ምርጫ ሳቢያ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚሊዮን እየተቆጠረ የተንቀሳቀሰው አንድን መንግሥት በፈለገውና ባሻው ሌላ መንግሥት ለመተካት ብቻ አልነበረም:: ህልማችን በቅድመ-ግንቦቱ ወቅት የነበረው የዴሞክራሲ ፍንጭ ሰፍቶና ሥር ሰዶ አገራችን ሰብዓዊ መብቶች ያለአንዳች መሸራረፍ የሚከበሩባት፥ የሕግ የበላይነት በተገዥዎች ላይ የሚጫን የገዥዎች መመጻደቂያ ሳይሆን በሁሉም ተከብሮና ተረጋግጦ አገራችን ተጠያቂነትን ባመኑና በተቀበሉ መሪዎች የምትመራበት ሥርዓት ለመፍጠር፥ ኅብረተሰባችንን ለዘመናት ሲያደማ ከቆየው የአመፅና የአሸናፊ/ተሸናፊ አዙሪት ወጥተን በብሔራዊ እርቅ ፖለቲካ የተረጋጋ ኅብረተሰብ ለመፍጠር፥ በመከባበር፥ በእኩልነት፥ በወንድማማችነትና በትግግዝ መንፈስ ከብረት ጠንክሮ ለሚገነባ የአገር አንድነት መሠረት ለመጣልና በነዚህ ሁሉ እሴቶች እውንነት ተመርኩዞ ሕዝባችን ዝንታለም ተውተብትቦ ከሚማቅቅበት የጥፋት አዙሪት ለአንዴም ለዘላለሙም ተላቆ ወደ አገር ግንባታና ልማት፥ ወደ ማኅበራዊ ፍትኅና ብልጽግና ያተኮረ ኅብረተሰብ የመገንባት ህልምና ተጋድሎ ነበር::

ይስፈኑ፥ ይዳብሩ እንላቸው የነበሩት ሰላምና ዴሞክራሲ ዛሬ ከቅድመ-ግንቦቱ ወቅት ይልቅ ከነጭራሹ ደብዛቸው እየጠፋ ነው:: በቅድመ-ግንቦቱ ወቅት በቋፍ ላይ የነበረው ነፃው ፕሬስ ዛሬ ሽታውም የለ:: በቅድመ-ግንቦቱ ዘመን "በተራ" የአፈና አገዛዝ ተሰማርተው የነበሩት ጥቂቶች ዛሬ በሽብር ብቻ ለመግዛት የተገደዱበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል:: በቅድመ-ግንቦቱ ወቅት የነበረችው የተጠያቂነት ፍንጭ መንምና ድኅረ-ግንቦት ወጣቶች በደርዘን ሽህ እየታፈሱ ቁጥራቸው፥ መዳረሻቸው፥ የሚፈለጉበት ወንጀል በውል ባልታወቀበት ሁኔታ በየማጎሪያ ጣቢያ መወርወራቸውቀጥሏል:: ወላጆች ቢያንስ ልጆቻችንን የት እንዳደረሳችኋቸው ንገሩን ብለው ለሚያሰሙት እሮሮ ጆሮ ዳባ ልበስ ተብሎ በሰኔና በጥቅምት ለተፈጸመው ግፍ ምንም እልባት ሳይገኝ ሌላ የወጣቶች አፈሳ ዙር እየተካሄደ ነው:: በአገራችን ታሪካዊ ተገቢነት ያለውን የብሔ/ብሔረሰቦች እኩልነትና ወንድማማችነትን ጥያቄ ድሮም ቢሆን ለመነገጃ ሲጠቀሙበት የቆዩት የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ መሪዎች አሁን ደግሞ በፋሽስታዊ ግፍ አፍነው የያዙትን የትግራይ ሕዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ወገኑ/ወንድሙ ነጥለው ለማናከስ ሃፍረትም ሆነ ይሉኝታ በማያውቅ ተራ ፕሮፖጋንዳ ሲንቀሳቀሱ እየታዘብናቸው ነው:: ይኸን ሁሉ ስናይ የምንደርስበት አንድ መደምደሚያ ላይ ብቻ ነው:: በእርግጥ ኢትዮጵያችን ከዛሬ ዓመት ዛሬ በየአቅጣጫው ወደኋላ እየሄደች ትገኛለች::

ይኸ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ መሪዎች ሕዝብን በጉልበት አፍኖ ለመያዝ የሚደረግ ሙከራ ግን ምንም ዘላቄታዊነት የሌለውና የአተርፍ-ባይ አጉዳይ ሂደት መሆኑ አይቀሬ ነው:: የግንቦት አንቀሳቃሽ እሴቶች ሚሊዮኖች ያነገቧቸውና ሊታገሉላቸውና ሊሰውላቸው የቆረጡባቸው እሴቶች ናቸውና፥ በዓለም-አቀፍ ደረጃም ቢሆን ሁሉም ቆሜላቸዋለሁ የሚላቸው በመሆናቸው ይኸ የኋሊት ጉዞ በጣም ጊዜኣዊ ክስተት ነው:: በአፈና አገዛዝ ላይ በቃኝ ብሎ የተነሳን ሕዝብ በሌላ ተጨማሪ አፈና መብታችን ብለው የተነሱ ሚሊዮኖችን በለየለት ዓይን ያወጣ የጉልበት አመፅና በሽብር ተቋቁሜ ድል አደርጋለሁ የሚለው የፀረ-ሕዝቦች ቅዠት ነው:: አይሠራም:: ቢሠራ ኖሮ እስከዛሬ በየትም አገር ያለ ማንም ሕዝብ ምንም ጊዜ ቢሆን ታግሎ ነፃነቱን የሚጎናፀፍበት አንዳች ተአምር አይኖርም ነበር:: ይኸ ቢቻል ኖሮ በዓለም ላይ ነፃ ሕዝብ መኖሩ ያጠራጥር ነበር:: የቆረጡ ሚሊዮኖችን ፀረ-አፈና ሕዝባዊ ትግል በጥቂቶች አፈና ብርታት ለመቋቋም መሞከር አሣን ውሃ ውስጥ እደፍቃለሁ (አሰምጣለሁ) ብሎ እንደመግደርደር ያኽል ከንቱ መፍጨርጨርና መታከት ነው::

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246, U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217 (Fax) 202-291-7645

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ከሰኔ ወር ጀምረን በተጨባጭ የምናየው እውነታ ይኸው የግፍና የትግል እንቅስቃሴ ተያይዞ የማየል ሂደት ነው። ጭፍጨፋ የሚሊዮኖችን ሕዝባዊ ትግል መግታት ቢችል ኖሮ ተጋድሎአችን በሰኔው የኢሕአዴግ መሪዎች ፀረ-ሕዝብ የግፍ እርምጃ ማግስት ባከተመ ነበር። ይኽ አልሆነም። ሰኔ ጥቅምትን ወለደ። ይኽንንም በደም አጥለቅልቀን እንወጣዋለን ያሉት ጥቂት የአገዛዙ ፀረ-ሕዝቦች እንደገና የንፁኃን ደም በግፍና በገፍ እንዲፈስ አደረጉ። እንደተመኙት ሕዝባችን አልተንበረከከላቸውም። ሕዝባዊ ተጋድሎው ከታሕሣስ ጀምሮ እንደገና አገረሸ። ዛሬ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ መሪዎች መጠን የሳተ የግፍ አመፅ በሕዝባችን በተለይም በወጣቱና በተማሪው ላይ እንደገና እየወረደ ነው። ይኽም አይሠራም። የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ መሪዎች ገባቸው አልገባቸው፥ ተቀበሉት አልተቀበሉት ትጥቅ ያስፈቱ እየመሰላቸው ጋፍኛ እያበራከቱ የሚሄዱት ግፍና አፈና ከድጥ ወደማጥ ጉዞ ስለሚሆንባቸው በየዕለቱ ይበልጥ ታጋይ፥ ከታጋይም የወሰነና የቆረጠ ታጋይ እየፈለፈለ እስከመጨረሻው ድል የሚቀጥል  ሕዝባዊ ትግል መቀስቀሱ አይቀሬ ሂደት ነው።

ወጣቱና ተማሪው በቃኝ፥ ተንገሸገሽኩ፥ አሻፈረኝ ብሎ በያለበት መነሳሳት መቀጠሉ የጥቂቶች "ሴራ" አይደለም። ማንም ሊገታው የማይችል የአኩሪው የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ወጣቶች ንቅናቄ ቅርስ ግፊት ነው። ይቀጥላል። እናት አባት ልጆቻቸው በብዙ ሽህ እየተቆጠሩ ደብዛቸው ሲጠፋ "የት ደረሱ" ብለው እነሱም በብዙ ሽህ እየተንቀሳቀሱ መጠየቃቸው አይቀሬ የወላጅ አንጀት የሚጠራው ተፈጥሮአዊ ግዴታ ነው። ዛሬ ሁሉም ቤቱን ዘግቶ ቢያለቅስ ነገ ሁሉም በአንድ ላይ ተነስቶና አደባባይ ወጥቶ ወንጀለኞቹ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይጠይቃል። ለጅምላ መቃብር የተዳረጉት ዜጎቻችንም "በሹም የታዘዘ" አፈር እንደለበሱ አይቀሩም። በመቶ ሽህ የሚቆጠር ዘመድ አዝማድ በያለበት ከተጣሉበት አንስቶ በክብር ለማሳረፍ መንቀሳቀሱ በባህላችን የተከበረውና የተቀደሰው እርም የማውጣት መብትን የማስከበር ጉዳይ ስለሆነ  ምንም ዓይነት ፀረ-ሕዝብ የጉልበት አመፅና አምባገነናዊ የሽብር ጦርነት ሊገታው አይችልም። ተቃዋሚን ደግፈሃል በሚል ውንጀላ ነጋዴው ሱቁ ሲታሸግ፥ ታክሲ ነጅው የሥራ ፈቃዱን ሲቀማ፥ ጎዳና ተዳዳሪው ወጣት ድህነቱና ዕድሜው ከወንጀል ተቆጥረውበት ከያለበት ሲታፈስ፥ ሠራተኛው ሥራ ማቆም አድማ ተሳትፈሃል ተብሎ ከሥራው ተፈናቅሎ ከሚስቱ፥ ከልጆቹና ከነመላ ቤተሰቡ ጉረሮው ሲዘጋ፥ ወዘተ... <u>ይኽ ሁሉ ከመብትም፥ ከዴሞክራሲም፥ ከአገር ክብርም አልፎ የጎልውና ጥያቄ አፍጥጦና አግጥጦ እንዲቀርብ ያደርገዋል</u>። ይኽ ደግሞ ከሕወሓት/ኢሕአዴግ ግፍ ጋር ተያይዞ እያየለ የሚሄድ የተቃውሞ ትግል መስፋቱና መጠናከሩ ሳይታለም የሚፈታ ጉዳይ ነው። ለዜጎች እኩልነት መከበር፥ ለነፃው ፕሬስ ማበብ፥ ለተጠያቂነት መስፈን፥ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር፥ ለሕዝብ ወንድማማችነት መጠንከር፥ ለሕግ የበላይነት መረጋገጥ፥ ወዘተ... ሕዝባዊ ዓላማዎችና ቁም ነገሮች ለአሥራ አምስት ዓመታት በውጭም በውስጥም ሲዋደቅ የቆየው አገር-ወዳድና ዴሞክራት በሚሊዮን የሚቆጠር ኃይል ነው። ይኽ ታጋይ ኃይልም ቢሆን አነሰ ያለው ሲቀነስበት እንቅስቃሴውን ማፋፋሙና መቀጠሉ ዴሞክራትነቱ፥ አገር ፍቅሩ፥ በሕዝብና በታሪክ ፊት አለብኝ የሚለው የኃላፊነት ስሜቱ የሚጭንበት ግዴታ ነውና ትግሉ ይቀጥላል፤ በተጠናከረ መልኩ።

መጭው ጊዜ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ መሪዎች በዚህ መልክ በአገር ውስጥ በሕዝብ ትግል ከዕለት ዕለት ከወር ወር ይበልጥ እየተጨነቁና እየባነኑ የሚሄዱበት ወቅት ብቻ አይደለም። ከድጡ ወደማጡ እያሉ የተያያዙት የጥፋት ጉዞ በዓለም-አቀፍ ደረጃም ይቀጥላል። ጥቂቶች በአገራችን ላይ የተከሉት የወስላቶች "ዴሞክራሲ" ከአሥራ አራት ዓመታት መመፃደቅ በኋላ በመላው ዓለም ሕዝቦች ፊት እርቃኑን ቆሞ መታየት ጀምሯል። የክስረትና የውርደት ሂደታቸው ምርጫን ዓይን ባወጣ ሁኔታ ሲያጭበረብሩ በተከሰተው ወገዛ ተከፈተ። ሰኔ ላይ የሕዝብ ድምፅ ይከበር ብሎ በተነሳው ሕዝብና በተለይ በወጣቱ ላይ ባደረሱት ግፍና ጭካኔ የተሞላበት ጉዳት ከየአቅጣጫው ተወግዘው ለአሳዳሪዎቻቸው ሳይቀር አሳፋሪ መሆን ጀመሩ። ጥቅምት ላይ በሌላ የግፍ አዙሪት ላይ ተሰማሩ። ትላንት "አዲስ የዴሞክራሲ መሪዎች ትውልድ" እየተባሉ ይሞካሹ የነበሩትን እነ አቶ መለስ ዜናዊን የውጭው ዓለም ከእንግዲህ ከተራ ወገዛ አልፎ ይጠየፋቸው ጀመረ። አራት መቶ ሚሊዮን

የሚጠጋ ሕዝብ የሚወክለው የአውሮጳ ፓርላማ ያሳለፈው ውሳኔ ባለፉት ዓመታት እንደለመድነው የሰብዓዊ መብቶችን እረገጣ በማውገዝና የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በመጠየቅ አያቆምም፤ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን መሪዎች ከሕዝብ ዘርፈው በውጭ ባንኮች ያስቀመጡት እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ፤ እነሱም ቢሆኑ ከእንግዲህ በአውሮጳ ኅብረት አባል በሆኑ አገሮች ድርሽ እንዳይሉ ቪዛ እንዲከለከሉ፥ ባለፉት ወራት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስለተፈፀመው ግፍ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አቀነባባሪነት አንድ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን እንዲቋቋም፥ ስለታሰሩትና ስለተገደሉት ዜጎች የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ይፋና ዝርዝር መግለጫ እንዲሰጥ፥ ወዘተ... የሚጠይቅ ውሳኔ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የዓለም ባንክና የአውሮጳ ኅብረት በጋራ በወሰዱት ፀረ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ መሪዎች እርምጃ እስካሁን ለበጀት ማሟያ እየተባለ ለአቶ መለስ መንግሥት በየዓመቱ በቀጥታ ይሰጥ የነበረው 375 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲቋረጥና ለሕዝቡ የሚያስፈልገው ይኸ ገንዘብ በሌሎች ይበልጥ ተኣማኒነት ባላቸው ወገኖች አማካይነት ወጭ እንዲደረግ መወሰናቸው ተነግሯል፡፡

ይኸ በሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አገዛዝ ላይ በውስጥም በውጭም እየደረሰ ያለ አይከስሩ ክስረት ብቻውን የነፃነታችንን ዋዜማ አያበስርም፡፡ ከፊታችን ገና ብዙ ትግልና መስዋዕትነት ይጠብቀናል፡፡ የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ መሪዎች የሚጨብጡትን አሳጥቶ የሚያናጫቸውና የሚያናክሳቸው ሕዝባዊ ትግል ከእንግዲህ ይበልጥ ተቀነባብሮና ተፋፍሞ በአገር-አቀፍ ደረጃም በውጭው ዓለምም መቀጠሉ ወሳኝ ነው፡፡ ይኸንን ታሪካዊ ተጋድሎ አስተባብረውና አቅጣጫ ሰጥተው የሕዝቡን ትግል ለድል ለማብቃት በመዋደቅ ላይ የሚገኙ የፖለቲካም ሆነ የሲቪክ ድርጅቶችና ስብስቦች፥ ተማሪው ሆነ ነጋዴው፥ ታክሲ ነጅው ሆነ ምሁሩ፥ ገበሬው ሆነ ሰራተኛው፥ ወጣቱ ሆነ አዛውንቱ ተራ በተራ እየተነሱ ተራ በተራ በሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪዎች ከሚጠቁበት ሂደት ይልቅ ሁሉም በአንድነት ለአንድ የጋራ ዓላማ እየተነሳ በተቀነባበረና በተቀናጀ መልክ እንዲታገል በተደጋጋሚ ጥሪ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ በእርግጥም የሕዝባችን ተጋድሎ ከአስከፊ ሽንፈት ተርፎ ለኢትዮጵያችን አዲስና ብሩኅ ምዕራፍ የሚከፈተው በትግል አንድነት ብቻ ነው፡፡ ይኸ ተደጋጋሚ ጥሪ አጉል ልፊፋ እንዳይሆን የሚፈልጉ ግንባር ቀደም አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች ሕዝባችንን ለትግል አንድነት ሲጠሩ መጀመሪያ እራሳቸው ይኸንን የትግል አንድነት ፈጥረው በአርኣያነት መታየት ይኖርባቸዋል፡፡ ግንባር-ቀደም ኃይሎች ተበታትነው አንዱ ወደ አራምባ አንዱ ወደ ቆቦ እያመላከቱ እዛው በዛው ደግሞ ሕዝብን በአንድነት እንዲታገል የሚቀርብ ጥሪ ከአንገት በላይ የሚደረግ ምንም ተአማኒነት የማይኖረው አካሄድ ስለሚሆን በሕዝቡ ትግል ላይ አሉታዊ ጫና ያሳድራል፥ ትግሉን ያቀጭጨዋል፥ ያሚዝዘዋል፡፡ ይኸንን የትግል አንድነት ለመፍጠር ከተፈለገ ደግሞ የኅብረታችን ሁለተኛ አስቸኳይ የሸንጎ ጉባዔ ውሳኔ በትክክል እንዳስቀመጠው ዛሬ የተያያዝነው ተጋድሎ የዚህ ወይም የዚያ የፖለቲካ ድርጅት፥ የዚህ ወይም የዚያ የሲቪክ ስብስብ፥ የዚህ ወይም የዚያ ግለሰብ ጉዳይ ሳይሆን በጠቅላላው በኅብረተሰባችን ውስጥ ያሉ የፖለቲካና የሲቪክ ኃይሎች፥ የወጣቶች፥ የሴቶች፥ የነጋዴዎች፥ የወላጆች፥ የተማሪዎች፥ የሠራተኞች፥ የገበሬዎች፥ የምሁራን፥ የወታደሮች፥ በውጭም በውስጥም ያሉ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳዶች ሁሉ የጋራ ተጋድሎ እንደሆነና ዛሬ ባለንበት ወሳኝ የትግል ምዕራፍ ጠባብና ወገናዊ፥ ድርጅታዊና ቡድናዊ አመለካከትም ይሁን ወገንተኝነት፥ አንጃኛነት አመለካከት፥ አስተሳብሰና ስሊቶች ቦታም ትርጉምም እንደሌላቸው ጠንቅቆ መረዳትና የአገሩቱን ሁኔታና የሕዝቡን ሰቆቃ ያገናዘበና ለሱም የሚመጥን የጋራ ምላሽ መስጠት አማራጭ የሌለው የወልና ዜጋዊ ግዴታ እንደሆነ ማጤን ያስፈልጋል፡፡

የኅብረቱ (ኢዴኃኅ) ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሁለተኛ አስቸኳይ ጉባዔ ከዚህ ግንዛቤ በመነሳት አንድነታችሁን አጠንክራችሁ ትግሉን አፋፍሙ ለምንላቸው ወገኖቻችን እኛ እራሳችን በምሳሌነታችን አመራር መስጠት የሚያስችለን ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ በአስቸኳይ እንዲጠራ የሚጠይቅ ታሪካዊ ጥሪ አስተላልፏል፡፡ ይኸ የኅብረቱ (የኢዴኃኅ) ጥሪ ብቻ አይደለም፡፡ የዘመናት ግፍ በቃን፥ ጭቆና በቃን፥ ክፍፍል በቃን፥ ድምፃችን፥ መብታችን፥

ኅልውናችን ይከበር ብለው፥ ዛሬ በሕወሓት/ኢሕአዴግ ዕብሪተኛ መሪዎች በታወጀብን የሽብር ጦርነት ምክንያት በየዕለቱ የሕይዎት፥ የደም፥ የእንባ፥ የእስራት፥ የግርፋትና የወከባ ግብር እየከፈሉ ለወራት ትግሉን ኅያው አድርገው የጠበቁትና ዛሬ ከአስከፊ ሽንፈት ለመትረፍ የአመራር ያለህ እያሉ በመጮህ ላይ ያሉ ሚሊዮኖች ጥሪ ነው፡፡ ይኸንን የሚሊዮኖች ጥሪ እውን ለማድረግ በኅብረቱም ሆነ በቅንጅቱ የተካተቱ ሕዝባዊ ትግሉን ለመቀጠል የቆረጡ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች፥ የነዚህ ድርጅቶች የድጋፍ አካሎች ተጠሪዎች፥ ኦነግን ጨምሮ የሌሎች ፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች፥ የመምሕራን፥ የጋዜጠኞች፥ የሴቶች፥ የወጣቶችና የሌሎች የሲቪኩ ማኅበረሰብ ስብስቦች፥ እንደዚሁም በያለበት "የሕዝብ ድምፅ ይከበር" ብለው በመታገል ላይ ያሉ የዜጎች ስብስቦች በአስቸኳይ ተገናኝተውና መክረው በአንድ በኩል ኢሕአዴግ/ሕወሓት በሕዝብ ላይ ያወጀውን የሽብር ጦርነት በጋራ ለመቋቋምና የድርጅት መሪዎች፥ ጋዜጠኞች፥ በአጠቃላይ በግፍ የታሰሩ ወገኖቻችንን በአስቸኳይና ያለ ምንም ቅድመ-ሁኔታ ለማስፈታት ሕዝባዊ ትግሉን ከሽንፈት ለማትረፍ ላለንበት የቀውስና የቀውጢ ወቅት የሚመጥን የጋራና የተቀናበረ እንቅስቃሴ ለማድረግ አንድ የጋራ ግብረ-ኃይል ማቋቋም፤ በሌላ በኩል በአገራችና በሕዝባችን የጋራ ኅልውና ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለማስወገድና ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተወሳሰቡ የመጡ መሠረታዊ ችግሮቻችንን በጋራ ለመመርመርና ዘለቄታዊ መፍትሔ በጋራ ለመሻት ሁሉም በጋራ የሚመክርበትና የወደፊት አቅጣጫችንን በተመለከተ የጋራ ስልትና ስትራቴጂ ለመንደፍ እንዲቻል አንድ ሁሉን-አቀፍ አገራዊ ጉባዔ እንዲጠራ ሁኔታዎችን የሚያመቻች የጋራ አዘጋጅ አካል በጋራ የሚቋቋምበትን ዘዴ ማመቻቸት ኅብረቱ ይዋል ይደር የማይባል አገራዊ ግዴታ አድርጎ ያየዋልና እነሆ ለዚህ ተግባራዊነት ጥሪያችንን በድጋሜ ለሁሉም እናቀርባለን፡፡

ሽብር ይቁም!
የታሰሩ ዜጎቻችንን በአስቸኳይ ይፈቱ!!
የትግል አንድነታችን ይጠንክር!!!
ድል በጋራ ትግል!!!!
የሕዝብ ትግል ያቸንፋል!!!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት

ጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም